# የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ
# የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ የተመደበለትን የመደበኛና ካፒታል በጀት በፋይናንስ አዋጅ፣ ደንብ እና በተከታታይ በወጡ መመሪያዎች መሠረት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ ከዚህ ሪፖርት ጋር የተያያዙትን የ2011 በጀት ዓመት የሂሳብ ሪፖርቶች እና ማስታወሻዎች ኦዲት አድርገናል።

የሂሳብ ሪፖርቶቹን የማዘጋጀት የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶቹን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው ።

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ዓለምአቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን መሠረት በማድረግና የዋና ኦዲተርን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው። እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ ( የኦዲት አስተያየት) ለመስጠት ያስችለናል።

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በኤጀንሲው ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው ።

ኦዲቱ የተከናወነው የዓመቱን የሂሳብ እቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው።

የሚከተሉት የኤጀንሲው የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል።

- የገቢ /የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት
- የመደበኛና የካፒታል ወጪ ሂሳብ ሪፖርት
- የገውውር ሂሳብ ሪፖርት
- የተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት
- የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት
- የሂሳብ ማመዛዘኛ ሪፖርት

የኤጀንሲው የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፤ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ፤ ደንብና መመሪያ የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

## የወጪ ሂሳብ፤

1. የስልጠና ተሳታፊዎች ስልጠናውን መካፈላቸውን የሚገልፅ የሰዓት መቆጣጠሪያ ሳይቀርብ ለሥልጠና እና ለመስተንግዶ በድምሩ ብር 861,351.84 ወጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## የተሰብሳቢ ሂሳብ፤

2. በሂሳብ መደብ 4211 በተሰብሳቢ የተያዘ ለትምህርት ወደ ውጭ አገር ለሄዱ የመ/ቤቱ ሰራተኞች የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በወቅቱ ሳይወራረድ ከ1ዓመት እስከ 8 ዓመት የቆየ የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 847,669.23 ተገኝቷል፡፡

## የተከፋይ ሂሳብ፤

3. በሂሳብ መደብ 5058 በድምሩ ብር 18,856,888.66 የተጨማሪ እሴት ታክስ ሂሳቡ ተጣርቶ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መተላለፍ ሲገባው በተከፋይ በመያዙ የኤጀንሲውን የበጀት ዓመት የተከፋይ ሂሳብ ከፍ እንዲል ማድረጉ ታውቋል፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 3 በተገለጹት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሳ በእኛ አስተያየት የኤጀንሲው የሂሳብ መግለጫዎች ሰኔ 30 ቀን 2011 ዓ.ም. የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም፡፡

## ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች

4. ለመደበኛ ወጪ ለየፕሮግራሞቹ ከተፈቀደው በጀት ውስጥ ብር 254,210,134.64 (22%) ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ ታውቋል፡፡

ሌሎች ጉዳዮች

5. በኤጀንሲው የንብረት ማከማቻ ውስጥ አገልግሎት የማያሰጡና እንዲወገዱ የተጠየቁ ብዛት ያላቸው የቋሚ እቃዎች፣ የማናጀር ወንበሮች፣ የፀሀፊ ጠረጴዛ፣ የኮምፒውተር ጠረጴዛ የእንጨት ሼልፍ፣ የእንግዳ ወንበር፣ የተሽከርካሪ ወንበር ሲሊንደር ትንሹ ወዘተ በኤጀንሲው የንብረት ማከማቻ መጋዘን ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

6. የኤጀንሲው ንብረት የሆኑ ብዛታቸው አምስት(5) ከመከላከያ የመጡ መኪናዎች ሊብሬ የሌላቸው መሆኑ፤

7. በኤጀንሲው ጋራዥ ውስጥ እና በቢሾፍቱ ጋራዥ ውስጥ በከባድና ቀላል ብልሽት ምክንያት እንዲሁም በመለዋወጫ ችግር ምክንያት የመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች የሰሌዳ ቁጥር 4-13652 ከ4ዓመት በላይ የቆመ ፣ የሰሌዳ ቁጥር 4-13653 ሚኒባስ መኪና ከ3 ዓመት በላይ የቆመ ፣ የሰሌዳ ቁጥር 4-21451፤ 4-20612 ለ11 ወር ያህል የቆሙ ተሽከርካሪዎች መኖራቸው ተረጋግጧል፡፡

ከሠላምታ ጋር